# ሐሰተኛ መሪዎች

## ጥበብ፣ ማሳሰቢያ፣ እና መመሪያዎች

MentorLink
INTERNATIONAL

Copyright © 2019 by MentorLink International

# ሐሰተኛ መሪዎች

## ጥበብ፣ ማሳሰቢያ፣ እና መመሪያዎች

- ሐሰተኛ መሪዎች እነማንናቸው?
- ምን ያነሳሳቸዋል?
- አገባባቸው እንዴት ነው?
- እንዴት ተፅዕኖ ያደርጋሉ?
- አስተምህሮአቸው ምንድን ነው?
- ምን ይደርስባቸዋል?
- ምላሽ እንዴት እንስጥ**?**
- ትኩረት ልንሰጣቸው የሚገባን የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?

## ፀሎት

እግዚአብሔር ሆይ፤ በውስጤ እውነትን ልታገኝ ይገባሃል። በሥጋዊ አይኔ አንተን በማያስከብር ልማዶችና አስተሳሰቦች ማየት ተስኖኝ እንደሚችል እናዘዛለሁ። በህይወቴ እና በእኔ አካባቢ ያሉ ሰዎች ሁላችንም ትኩረታችን በአንተ ላይ እንዲሆን እፈልጋለሁ። በህይወቴ እና በአገልግሎቴ ይህንን ርዕስ መተግበር እንድችል የሚረዳኝ ፀጋ እና ጥበብ እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ። በዙሪያዬ ያለውን የስህተት ነገር ማየት እንድችል አይኖቼን አብራልኝ። የሀሰት መሪዎች በሌሎች ላይ ተፅዕኖ እንዳደርግ አድርገውኝ ከሆነ ወይም ሊያደርጉኝ ከፈለጉ መንፈስህ እንዲገልጥልኝ እፀልያለሁ። እግዚአብሔር  ሆይ አንተን ከፍ ላደርግህና ላከብርህ እወዳለሁ። በኢየሱስ ስም፤ አሜን።

---

ይህንን ጥራዝ ለሌሎች እንድታሰራጩ እናበረታታችኋለን። ኤሌክትሮኒክ ቅጂ ከፈለጉ ከሚከተለው ድረ-ገፅ ማግኘት ይችላሉ www.MentorLink.org. ይህንን ፅሁፍ ያለምንም ለውጥ ማባዛትና ማሰራጨት ይፈቀዳል።

Copyright © 2019 ሜንተርሊንክ ኢንተርናሽናል

ሜንተር ሊንክ ኢንተርናሽናል የአሰልጣኞች፣ የመሪዎች፣ የአገልግሎቶች፣ የአብያተክርስትያናት፣ የቤተዕምነቶች ድር እንቅስቃሴ ሲሆን "እንደ ኢየሱስ የሚመሩ መሪዎችን" የማፍራት ስራ እየሰራ ይገኛል።
ከእናንተ መስማት እንፈልጋለን። ማንኛውንም ጥያቄ እና አስተያየቶች ወደ FalseLeaders@MentorLink.org ኢ_ሜይል አድርጉልን።

# ትኩረት የሚፈልጉ የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?

ሠይጣን የማታለል አባት ነው። ዓለምን ይቆጣጠራል እንዲሁም የክርስቶስ የሆኑ ነገሮችን እንዳናይ ያሳውራል። እራሱን እንደ ብርሃን መልዓክ አድርጎ ሊገልጥ ይችላል። የእርሱ አገልጋዮችም የፅድቅ መሪዎች እንደሆኑ እንዲያስመስሉ ያደርጋል።. (ዩሐ. 8:41-47; 2 ቆሮ. 4:4; 2 ቆሮ. 11:13-14; ኤፌ. 2:2; ኤፌ. 6:12)

ኢየሱስ እና ደቀመዛሙርቱ ሀሰተኛ መሪዎች ተመሳስለው ገብተው ቅዱሳንን ሊያስቱ እንደሚችሉ አስጠንቅቀዋል። ወንጌላት፣ የሐዋርያት ሥራ፣ እንዲሁም ፊልሞና እና ያዕቆብ በስተቀር ሁሉም የአዲስ ኪዳን መፅሀፍት ስለ ሀሰተኛ መሪዎች ይናገራሉ። (ማቴ. 24:5, 24; ሐዋ 20:29-31)

ሀሰተኛ መሪዎች አራቱን ወሳኝ መፅሀፍ ቅዱሳዊ እውነታዎች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ይክዳሉ:

1. ሥላሴ፤ አንድ እግዚአብሔር፣ ሦስት አካል፣ እኩል አምላክነት (ማቴ. 28:19; ዩሐ. 6:27; ዩሐ. 16:5-11; ሐዋ 5:3-4; 2 ቆሮ. 13:14; ዕብ. 1:8)
2. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ፤ የሞተው፣ የተቀበረው ደግሞም የተነሳው አሁን ደግሞ በአብ ቀኝ የተቀመጠው ደግሞም የሚመጣው። እርሱ ይህይወታችን እና የአገልግሎታችን ዋና ትኩረት ሊሆን ይገባል። በምድርና በሠማይ ሥልጣን ሁሉ ለእርሱ ተሰጥቶታል። (ማቴ. 28:18; 1 ቆሮ. 1:23; ቆላ. 1:15-23; ቆላ. 3:1-4; 1 ዩሐ. 4:1-6; ራዕ. 1:7)
3. በክርስቶስ ሥራ እና ህይወት ላይ ትኩረት ያደረገው በሮሜ፣ ገላትያ እና ሌሎች ክፍሎች የተቀሰው ወንጌል ግልፅ እና ትክክል መሆን አለበት። (ሮሜ. 1:1-16:27; ገላ. 1:6-10)
4. አዲስ ኪዳን እና ብሉይ ኪዳን መሪዎችንና፣ ትምህርታቸውን የምንዳኝበት ብቸኛ መንገዶች ናቸው። (2 ጢሞ. 3:16-17; 2 ጴጥ. 3:16)



## መግቢያ

ማታለል በመፅሀፍ ቅዱስ ቃላት ታጅቦ እና ተቀምሞ በጣም በሚስቡ መልዕክተኞች ይቀርባል። እናም ልክ እንደ ተላላፊ ወረርሽኝ በአንድ ጊዜ ይዛመታል።

በመጨረሻው ዘመን አታላዮችና ስራቸው እየበረከተ እንደሚመጣ ሐዋርያትና እራሱ ክርስቶስ አስተምረዋል። ማንም ቢሆን በእንደዚህ አይነቶች ሀሰተኛ አስተማሪዎች ሊታለል ይችላል። ሐዋርያትና ክርስቶስ፣የመንግስቱ መሪዎች ምን መሆን እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው አስተምረዋል። ኢየሱስ አማኞችን ለዚህ ሁሉ ነገር ተጠያቂ ያደርጋል። ሐሰተኛ አስተማሪዎችን ደግሞ በፅድቅ ይፈርድባቸዋል።

እኛ* ሁላችን የጌቶች ጌታ የሆነውን ክርስቶስን በተግባርና እርሱን በሚመስል ልብ ልንመስለው እና ልንከተለው እንፈልጋለን። እንዲሁም ደግሞ የክርስቶስ ሙሽራ የሆነችው ቤተክርስትያን ታድግ ዘንድ ሌሎች እንደ እኛ እንዲሆኑ እንፈልጋለን።

የክርስቶስ ወንጌል በንፅህና ይሰፋ ዘንድ ሁላችንም ሽክም አለብን። የሀሰተኞች ትምህርት ከክርስቶስ ወንጌል እና ከመንግስቱ ሥራ ላይ ትኩረትን ሊሰርቅ ይችላል የሚል ሥጋት ይኖረናል። እንደነዚህ ያሉ አደገኛ እውነታዎች ከፍተኛ የሆነ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

## ግባችን

1. አማኞች ሀሰተኛ መሪዎችን በቀላሉ እንዲለዩና እርምጃ እንዲወስዱ የሚያስችሉ ነገሮችን በዚህ መፅሀፍ በኩል መስጠት
2. አዲስ ኪዳን ስለ ሀሰተኛ መሪዎች የሚናገረውን አለማቀፋዊ ተቀባይነት ያለውን አስተምህሮ መስጠት
3. በመርህ ላይ የተመሰረተ፣ የግል አስተያየት መስጠት የሚያስችል እና በቀላሉ ለመረዳት በሚያስችል መንገድ ይህንን ጉዳይ ማሳየት
4. መሪዎች ታማኝ ወደሆነ እና ክርስቶስ ላይ ትኩረቱን ወዳደረገ አመራር እንዲመጡ ማበረታታት. (ክርስቶስን የሚመስል መሪነትን በቀላሉ ለመመልከት The Leader's Covenant የሚለውን ይመልከቱ)

## ፀሎት

እግዚአብሔር ሆይ፤ በውስጤ እውነትን ልታገኝ ይገባሃል። በሥጋዊ አይኔ እንተን በማያስከብር ልማዶችና አስተሳሰቦች ማየት ተስኖኝ እንደሚችል እናዘዛለሁ። በህይወቴ እና በእኔ አካባቢ ያሉ ሰዎች ሁላችንም ትኩረታችን በአንተ ላይ እንዲሆን እፈልጋለሁ። በህይወቴ እና በአገልግሎቴ ይህንን ርዕስ መተግበር እንድችል የሚረዳኝ ፀጋ እና ጥበብ እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ። በዙሪያዬ ያለውን የስህተት ነገር ማየት እንድችል አይኖቼን አብራልኝ። የሀሰት መሪዎች በሌሎች ላይ ተፅዕኖ እንዳደርግ አድርገውኝ ከሆነ ወይም ሊያደርጉኝ ከፈለጉ መንፈስህ እንዲገልጥልኝ እፀልያለሁ። እግዚአብሔር ሆይ አንተን ከፍ ላደርግህና ላከብርህ እወዳለሁ። በኢየሱስ ስም፤ አሜን።

# ሐሰተኛ መሪዎች እነማን ናቸው?

ሀሰተኛ መሪዎች የምንላቸው ሰዎች ትኩረታቸውን ከኢየሱስ ላይ እንዲያነሱ መንገድ የሚያሳዩ ናቸው። በተጨማሪም የመፅሀፍ ቅዱስ አስተምህሮዎችን በማጣመምና በማሳነስ ቅዱሳን በፅምነት የተሞላ እና እግዚአብሔርን የሚመስል ኑሮ እንዳይኖሩ ይመራሉ። (1 ጢሞ. 6:3-5; 1 ዮሐ. 4:1-6; ይሁዳ 4)

ሌሎችን የሚመሩ 4 ዓይነት መሪዎችን እንመለከታለን

1. አንዳንዶች ተጨማሪ መረዳትን የሚፈልጉና ያልተማሩ ናቸው (ሐዋ18:24-28)
2. Sአንዳንዶች ዓለማዊ ፍልስፍና እና ልምምዶችን ያዘወትራሉ *(ማቴ. 6:1-18; 1 ቆሮ. 3:1-4; ገላ. 2:11-14; 2 ጢሞ. 4:10)*
3. አንዳንዶች የተታለሉ እና ውእነተኛ አማኞች ላይሆኑም ይችላሉ *(1 ቆሮ. 3:13-15; 1 ጢሞ. 6:3-5)*
4. አንዳንዶች የሀጢያት አባት በሆነው በአባታቸው ሰይጣን ይመራሉ *(ዮሐ. 8:44; 2 ቆሮ. 11:13-15)*

ሀሰተኛ መሪዎች በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደዚህ ተጠርተዋል:

- ሀሰተኛ ነቢያት (ማቴ. 7:15-23)
- የሠይጣን ልጆች (ዮሐ. 8:44)
- የማያስተውሉ ሞኞች (ማቴ.23:16-26)
- የእፉኝት ልጆች. (ማቴ. 23:33)
- ግብዞች (ማቴ. 23:1-36; ሉቃ.12:1-3)
- የሐሰት አስተማሪዎች (2 ጴጥ. 2:1)
- የሐሰት ሐዋርያት (2 ቆሮ. 11:12-15)
- ተንኮለኛ ሰራተኞች (2 ቆሮ. 11:12-15)
- የክርስቶስ ተቃዋሚዎች (1 ዮሐ. 2:18-22)
- አታላዮች (2 ዮሐ. 7-8)
- ብዙ ሌሎች አይነት ስያሜዎች (2 ጴጥ. 2:17; ይሁዳ 12-13)

***ማስጠንቀቂያ:*** *አንዳንድ ሰዎች የማንስማማበት አመለካከት እና አካሄድ ሊኖራቸው ይችላል፤ ነገር ግን ይህ ማለት ሀሰተኛ መሪዎች ናቸው ማለት ላይሆን ይችላል። በደንብ ለመረዳት የሚከተሉትን ክፍሎች እንመልከት* (ሉቃ. 9:49-50; ሮሜ. 14:1-12)

**ምላሽ ለመስጠት እና ለውይይት ጊዜ ውሰዱ:**

1. ሀሰተኛ አስተማሪዎችን እና አስተምህሮዓቸውን የመለየት ልምዱ ምን ይመስላል?
2. በሀሰተኛ መሪዎች የደረሰ ጉዳት የት ተመልክቻለሁ?
3. ይህ ርዕሰ ጉዳይ ለምን ለእኔ አስፈላጊ ሆነ?



**በግል የተለያዩ መመሪያዎች ተሰጥቶናል:**

- በፅድቅ ለመታረም እና ለመስተካከል ስልጠና ለመውሰድ እራሳችንን ማዘጋጀት አለብን (2 ጢሞ. 3:14-17; 1 ዮሐ.1:7-10)
- የሰይጣንን ፍላፃ ማጤን አለብን (2 ቆሮ. 10:3-4; ኤፌ. 6:10-18; ኤር. 4:7; 1 ጴጥ. 5:8)
- ኢየሱስ ከእኛ ከሚፈለገው ባህሪ እና ግንኙነት ጋር ህይወታችንን እንድናስታርቅ ታዘናል። በህይወታችን፣ በአገልግሎታችን እንዲሁም በአመራራችን ውስጥ ያለ ሀጢያትን መናዘዝ አለብን (2 ጢሞ. 2:22; 1 Jዮሐ1:9)
- የሀሰት መሪነት አዝማሚያ በሚታይብን ጊዜ እንድንነቃ እና ንስሀ ሊያስገቡን የሚችሉ መንገድን የሚያሳዩ ሰዎችን ወይም የታመኑ አማኞችን እንፈልግ። (2 ጢሞ. 3:10-17)

በአገልግሎታችን ውስጥ የሚከተሉት ነገሮችን ጥንቃቄ ማድረግ አለብን:

- ሌሎችን ስለ መታለል እና ስለ ሀሰተኛ መሪዎች ጉዳይ ማስጠንቀቂያ መስጠት. (ማቴ. 23:1-36; ሐዋ 20:28-31; 2 ጢሞ. 3:1-17)
- አማኞች እንደ ስህተት ሽንገላ ባለ ተንኮል በሰዎች ማታለልም በትምህርትን ንፋስ ምክንያት ወዲያና ወዲህ እየተፍገመገሙ ወደፊት ህፃናት እንዳይሆኑ ማስታጠቅ። (ኤፌ. 4:12-15; 2 ጢሞ. 4:1- 5; 2 ጴጥ. 3:1-18)
- የሀሰት ትምህርቶችን እና ሀሰተኛ መሪዎችን ለመለየት እንችል ዘንድ ከሌሎች ጋር በአገርነት መስራት (ሐዋ 15:1-11; ሐዋ 20:25-31)
- በውስጣቸው ክፋት የሌለባቸውን ነገር ግን በስጋ የተታለሉ ሀሰተኛ መሪዎችን ለመታደግ መፈለግ አለብን። እንደ እግዚአብሔር ቃል በመጀመሪያ ለብቻችን እናናግረዋለን ቀጥሎም ምንም ምላሽ ካልሰጠ ከሌሎች ጋር በመሆን እናናግረዋለን። (ማቴ. 18:15-17; ሉቃ. 17:1-4; ገላ. 2:11-21; ገላ. 6:1-5)
- ሀሰተኛ መሪዎችን በፍቅርና በጥንቃቄ ልንገስፅ፣ ልናበረታታ፣ ልናስተምርና ትምህርታቸውን ልናስጥላቸው ይገባናል። (ሮሜ. 16:17-18; 2 ጢሞ. 2:14-19; 2 ጢሞ. 2:24-26; ቲቶ.3:10; 2 ዮሐ. 7-11; 3 ዮሐ. 9-11; ይሁዳ 3-4)

**ምላሽ ለመስጠትና ለውይይት ጊዜ ውሰዱ:**

1. የኢየሱስን መንገድ ሊመስሉ የሚገቡ የህይወታችን ክፍሎች ምንድን ናቸው?
2. በዚህ ርዕስ ለመነጋገር የማምናቸው ሰዎች እነማን ናቸው?
3. ሌሎችን እያሳተ ያለ የሀሰት መሪ የማግኘት ዕድልን ባገኝ ምን እናገራለሁ?
4. ይህንን ትምህርት በእኔ ተፅዕኖ ሥር ያሉትን ለማብቃት እንዴት ልጠቀምበት እችላለሁ?

**ምላሽ ለመስጠት ወይም ለውይይት ጊዜ ውሰዱ:**

1. በእኔ ባህል ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ የሀሰት ትምህርቶች ምንድን ናቸው?
2. እነዚህ የሀሰት ትምህርቶች የመፅሀፍ ቅዱስን ታሪክ ባልተገባ ሁኔታ የሚጠቀሙት እንዴት ነው?
3. ይህ የሀሰት ትምህርት እንዴት ነው እኔን የሚያስጠነቅቀኝ ወይም የሚያነሳሳኝ?

## ምን ይደርስባቸዋል?

እግዚአብሔር ሀሰተኛ መሪዎችን ያስጠነቅቃል፣ ይቀጣል እንዲሁም ይኮንናል።

- ኢየሱስ ጌታ፣ ንጉስ እና ዳኛ ነው። ሁላችን እያንዳንዳችን በተቀመጠው መስፈርት መሰረት እንዳኛለን. (ዩሐ. 5:22-23; ፊል. 2:9-11; ኤር. 3:1)
- አንዳንድ ሀሰተኛ መሪዎች መሪዎች እውነተኛ አማኞች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን እራሳቸውን አስተዋል። ወደ እሳት ባህር ውስጥ ይጣላሉ በተጨማሪም አክሊላቸውን ያጣሉ። (1 ቆሮ. 3:12-15; 2 ዩሐ. 7-10)
- "ለእነርሱ ወዮላቸው." በክርስቶስ ያልሆኑ ሀሰተኛ መሪዎች (እግዚአብሔር ማን እንደሆኑ ያውቃቸዋል), "... ለእነርሱ ጥብቅ የሆነ ድቅድቅ ጨለማ ተዘጋጅቶላቸዋል". (ማቴ. 13:24-30; ማቴ. 13:36-43; ማቴ. 23:29-33; ፊል. 3:18-19; 2 ጴጥ. 2:3-10, 17, ይሁዳ 5-16) (ኢየሱስ በ ማቴ. 23 ላይ በሀሰተኛ መሪዎች ላይ ስላሳየው ቁጣ አስታውሱ። ከባድ በሆነ ሁኔታ ይፈርዳል።)

**ምላሽ ለመስጠት እና ለውይይት ጊዜ ውሰዱ:**

1. ኢየሱስ በሀሰተኛ መሪዎች ላይ በሚወስደው መኮነን የሚሰማኝ ምንድን ነው?
2. በኢየሱስ ፊት ለፍርድ የመቆም እውነታ ተግባሬን፣ አስተምህሮዬን እና ውስጣዊ ሀሳቤን እንዴት አድርጎ ነው የሚቀርፀው?
3. በገልፅ ተከታዮቻቸውን የሚያጭበረብሩ ሀሰተኛ መሪዎች ከሚጠብቃቸው የብርሃን ፍርድ አንፃር ያለኝ ስሜት ምንድን ነው?

## ምላሽ መስጠት ያለብን እንዴት እንዴት ነው?

ኢየሱስ እና ሐዋርያቱ ሀሰተኛ መሪዎች እንዴት መደረግ እንዳለባቸው ግልፅ የሆነ መመሪያ ሰጥተዋል። በአስተምህሮአቸው፣ ባህሪያቸው፣ የውስጥ ሀሳባቸው ተግባራቸው እና ተፅዕኖአቸው የሚያሳዩትን ስህተት ይገልፃሉ፤ እንዲሁም ከእነርሱ እንድንጠበቅ ያሳስባሉ። አልፎ አልፎም ስማቸውን በመጥቀስ ይገስፁአቸዋል።



## ምን ያነሳሳቸዋል?

ሀሰተኛ መሪዎች በርካታ በሀጢያት የተሞሉ ሀሳቦች አሏቸው:

- የሰይጣንን ሀሳብ መፈፀም ይፈልጋሉ (ዩሐ. 8:41-44)
- ሰዎችን በመቆጣጠር ስልጣንን መያዝ ይፈልጋሉ (3 ዩሐ. 9-11)
- የእግዚአብሔርን አገልጋዮችን እና የመፅሀፍ ቅዱስን ቃል ያቃልላሉ (ፊልጵ. 1:15-17; 2 ጴጥ. 3:16)
- ከሰዎች ክብርና ምሥጋናን ይፈልጋሉ (ማቴ. 23:5-7; ዩሐ. 12:42-43; ገላ. 1:10)
- ገንዘብ የሚያገኙበትን መንገድ ይፈልጋሉ (ዩሐ. 12:4-8; 2 ጴጥ. 2:3; 2 ጴጥ. 2:12-16)
- ዓለማዊ የኑሮ ዘይቤን ያንፀባርቃሉ (2 ጴጥ. 2:17-22)
- የራሳቸውን አስተምህሮ ያራምዳሉ (1 ጢሞ. 1:3-7)

የሀሰተኛ መሪዎች የውስጥ ሀሳብ በጊዜ ሂደት ውስጥ የሚገለጥ ይሆናል። የውስጣቸውን ሀሳብ ለማወቅ የአንደበታቸውን፣ የህይወታቸውን እንዲሁም የአገልግሎታቸውን ፍሬ አስተውሉ። (ማቴ. 7:15-20; ማቴ. 12:33-37; ገላ. 5:19-25; 1 ጢሞ. 5:24)

**ምላሽ ለመስጠት እና ለውይይት ጊዜ ውሰዱ:**

1. ባሳለፍኩት ጊዜ የሌሎችን የውስጥ ሀሳብ እንዴት ተረዳሁ?
2. "ፍሬ መመልከት" የሌሎችን የውስጥ ሀሳብ እንድመለከት እንዴት ይረዳኛል?
3. ፍሬ የውስጥ ሀሳብን የሚገልጥ ከሆነ የህይወቴ ፍሬዎች የሚገልጡት ምን ዓይነት የውስጥ ሀሳቦችን ነው?

1

## መግቢያ የሚያገኙት እንዴት ነው?

ሀሰተኛ መሪዎች በብዙ ዓይነት መንገድ በእኛ መካከል ይገኛሉ:

- በሚስጥር ሊገቡ ይችላሉ. (ሐዋ 20:28-31; 2 ቆሮ. 11:14-15)
- ሰዎችን አጓጊ በሆኑ ሥጋዊ ፍላጎቶች ይስባሉ (2 ጴጥ. 2:1-3; ይሁዳ 4)
- ሰዎች መስማት የሚፈልጉትን ይናገራሉ (2 ጢሞ. 4:3; 2 ጴጥ. 2:1-3)
- ደካማና ያልተረጋጉ ሰዎችን ይፈልጋሉ (2 ጢሞ. 3:6-7)
- እራሳቸውን እንደ ነፃ አውጪ ወይም ክርስቶስ እንደሆኑ ይናገራሉ. (ማቴ. 24:5)
- ለስለስ ያለ ንግግር ይጠቀማሉ. (ሮሜ. 16:17-18)
- በግለሰቦች ወይም በቡድን ድጎማ ይጠቀማሉ.(ገላ. 2:11-14)
- ክርስቶስን መከተል ሊያስተዉ የሚችሉ ዓለማዊ መርሆችን እና ጥበባትን ይጠቀማሉ. (ቆላ. 2:8)

**ምላሽ ለመስጠት እና ለውይይት ጊዜ ውሰዱ:**

1. ሀሰተኛ መሪዎች ወደ አገልግሎት በሚመጡበት ጊዜ እንዴት እለያለሁ?
2. በእኔ ባህል ውስጥ ሀሰተኛ መሪዎች ወደ አማኞች ህብረት የሚገቡት እንዴት ነው?
3. እንደዚህ አይነት ሰዎችን ስመለከት ምን ዓይነት ውስጣዊ የማስጠንቀቂያ ስሜት ይሰማኛል?

## ተግባራቸው ምን ይመስላል?

የሀሰተኛ መሪዎች ተግባር አደገኛ ነው:

- እራሳቸውን የፅድቅ አገልጋይ አድርገው ያቀርባሉ. (2 ቆሮ. 11:12-15)
- የእግዚአብሔርን ሥልጣን በሚያዋርድ ሁኔታ የተዛባ ፆታዊ ፍላጎትን ይከተላሉ (2 ጴጥ. 2:10; 2 ጴጥ. 2:18)
- እራሳቸውን እንደ አስፈላጊ ሰው በመቁጠር መጠሪያ እና ሥልጣን ለራሳቸው ይሰጣሉ. (ማር. 12:38-40; ሉቃ. 22:24-27)
- ባዶ ባህላዊ እምነቶችን እና ፍርሃቶችን በመጠቀም ሊሎችን እንደፈለጉ ያደርጋሉ. (ቆላ. 2:8)
- ዓለማዊ አስተሳሰቦችን በመጠቀም የመከፋፈል ስልትን ይጠቀማሉ (ይሁዳ 16, 19)
- ምድራዊ የአገዛዝ ሥልትን በመጠቀም ሥልጣናቸውን እና ቦታቸውን ያስጠብቃሉ. (3 ዩሐ. 9-11)
- የሚፈልጉትን ለማድረግ የሚማርክ ንግግር ያደርጋሉ. (ሮሜ. 16:17-18; ይሁዳ 16)
- ከሰዎች ምስጋና እና ክብር በመፈለግ የሰዎችን ትኩረት ወደራሳቸው ያደርጋሉ. (2 ቆሮ 5:12; ማቴ 6:1-18)
- ከፊት ለፊት ሲታዩ ታማኝ እና ሰውን ወዳድ ይመስላሉ፤ ነገር ግን ከበስተጀርባ አታላዩች ናቸው. (ማር. 12:38-40)
- የውስጣቸውን ፍላጎት ብቻ ይከተላሉ. (ፊል. 3:18-19)
- ስለ እራሳቸው ብቻ ግድ. (ይሁዳ 12)

**ምላሽ ለመስጠት እና ለውይይት ጊዜ ውሰዱ:**

1. በእኔ ባህል ውስጥ የሀሰተኛ መሪዎች ድርጊት ምን ይመስላል?
2. እንደ ሀሰተኛ መሪ የተመላለስኩበት ሁኔታ አለ?
3. ስለ ሀሰተኛ መሪዎች ያወቅሁት ነገር እንዴት ሊያነሳሳኝ ወይም ሊያስጠነቅቀኝ ይችላል?



## ሰዎች ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉት እንዴት ነው?

ሀሰተኛ መሪዎች ሰዎችን ይጎዳሉ:

- ሰዎችን አፍራሽ የሆኑ አመለካከቶችን እንዲቀበሉ ይደረጋሉ.(2 ጴጥ. 2:1)
- ከእግዚአብሔር ይልቅ የሀሰተኛው መሪ ደቀመዝሙር እንዲሆኑ ይታለላሉ. (ማቴ. 24:9-14; ሐዋ 20:29-30; 3 ዩሐ. 9-11)
- ዓለማዊ መንገዶችን እንዲከተሉ ይገደዳሉ. (2 ጴጥ. 2:2; 2 ጴጥ.2:17-19)
- በማንገላታት፣ በመራርነት፣ በተቃውሞ፣ በቁጣ ፣ በጥርጣሬ እንዲሁም በግጭት የተሞሉ ናቸው። (1 ጢሞ. 6:3-5; 2 ጴጥ. 2:14-19)
- ከክርስቶስ እንዲርቁ፣ እውነትን እንዲቃወሙ እንዲሁም ዓለማዊ ምኞትን እንዲከተሉ ይገደዳሉ። (2 ጢሞ. 3:1-9)
- ሰዎች ግራ ይጋባሉ እንዲሁም ይበሳጫሉ (ገላ. 1:7; ገላ. 5:10; ቲቶ.1:10-11)

**ምላሽ ለመስጠት እና ለውይይት ጊዜ ውሰዱ:**

1. ሀሰተኛ መሪዎች በግለሰቦች ወይም በህብረት ላይ ምን ጉዳት ሲያደርሱ ተመልክቻለሁ?
2. ሀሰተኛ መሪዎች በእኔ ላይ ምን አይነት ጉዳት አድርሰዋል?
3. ይህ ጉዳት ምን አይነት ስሜት እንዲኖረኝ አድርጓል?

## ምን ያስተምራሉ?

ሀሰተኛ መሪዎች የተደበቀ ስህተትን፣ ግማሽ እውነትን እንዲሁም ውሸትን ያስተምራሉ:

- ትክክል ያልሆኑ አመለካከቶችን እና የሚፃረሩ አስተምህሮዎችን ያበረታታሉ (ቆላ. 2:8; 1 Jn. 2:18-24)
- የሀሰት አመለካከትን እንዲሁም ተቃራኒ ቀኖናዎችን ያበረታታሉ. (ማር. 7:1- 13; ሮሜ. 16:17-18; 2 ቆሮ. 11:3-4; 2 ጴጥ. 2:1)
- እውነትን ይቃወማሉ ወይም ግማሽ እውነት ላይ ያተኩራሉ. (1 ጢሞ. 1:3-7; 1 ጢሞ. 6:3-5; 2 ጢሞ. 3:8; 2 ጴጥ. 3:14-17)
- የመፅሀፉን ቃል ያጣምማሉ ወይም ለራሳቸው ዓላማ እንደሚመች አድርገው ይተረጉሙታል (ማቴ. 4:1-11; 2 ጴጥ.3:14-17)
- ከእግዚአብሔር መንገድ ይልቅ የዓለምን መንገድ ያደንቃሉ (ቆላ. 2:8; 2 ጢሞ. 2:16-18; 2 ጴጥ. 2:18-19)